# እውነትም “ያለበት” ይገንበት እንዳይሆን ?

May 22, 2013

*ከሙሼ ሰሙ(የኢዴፓ ፕሬዚዳንት)*

### “በዓለም ላይ ያሉ  ሃገሮች የራሳቸው መከላከያ ሰራዊት አላቸው፡፡ የኛ መከላከያ ሰራዊት ግን አልጄሪያ የሚባል የራሱ ሃገር አለው፡፡”

አዲስ አድማስ ጋዜጣ በዜና ዘገባው ላይ የመከላከያ ሳምንትን አስመልክቶ የፖለቲካ ፓርቲዎች አቋማችንን እንድንገልጽ እድል ሰጥቶን ነበር፡፡ በዚህ እድል ሃሳባቸውን ከገለጹት ተጋባዦች መካከል አንዱ እኔ ነኝ፡፡ ዜና ዘጋቢው ለአምዱ ስፋት ይመጥናል ባሉት ልክ ሃሳቤን ቀንጨብ አድርገው በማቅረባቸው በርካታ ሃሳቦቼ በዓምዱ ላይ የመካተት እድል ሊገጥማቸው አልቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት በአንባቢያን ዘንድ በቂ ግንዛቤ አልተፈጠረም የሚል ስጋት ነበረኝ፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዲስ አድማስ ሳምንታዊ ጋዜጣ ላይ የመከላከያ ሳምንትን አስመለክቶ በሰጠሁት አስተያየት ላይ “ጭስ የለውም እንጂ እሳቱስ አሪፍ ነው” በሚልና “የሠራዊት ቀንና የተቃዋሚዎች መሠረተ- ቢስ እሳቤዎች” በሚሉ ሁለት ርዕሶች ስር የተለያዩ ጸሐፊዎች ዘለፋና ዛቻ አዘል ትችቶች በአዲስ ዘመንና በአይጋ ድረ ገጽ ላይ  አቅርበዋል፡፡ በአጠቃላይ ተቺዎቼ የመከላከያ ሳምንት ኢግዚቢሽንን ከጎበኘሁ በኃላ ለመታዘብ በቻልኳቸው ሕጸጾች ላይ የሰጠኋቸውን ገንቢ አስተያየቶች የሚያጣጥልና አንደውም ምን ሲደረግና ሲታሰብ በመከላከያ ላይ አስተያየት ተሰጠ በሚሉ በብስጭቶችና ቁጭቶች የታጠሩ ናቸው፡፡

ስልጣን በምርጫ  አማካኝነት ይገኝ በሕገ ወጥ መንገድ በሕዝብ ሃብት ላይ እያዘዙ “የሹም ዶሮ ነኝ እሽ አትበሉኝ ” ማለት የማያዛልቅ ጸሎት ሊ—ከመሆን አይዘልም፡፡ ዜጎች በማንኛውም ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ መረጃ የማግኘት፣ ሃሳብ የመሰንዘር፣ የማዳመጥና ልዩነቶችን የመመርመር ዘለግ ሲልም የተሻለውን የመምረጥ መብት አላቸው፡፡ በተለይ ደግሞ በሕገ-መንግስታችን ላይ የሰፈሩት በርካታ ዓለም አቀፍ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ድንጋጌዎች ማንም ከሕዝብ ዓይንና ጆሮ ውጭ እንዲሆን እድል የሚሠጡ አይደሉም፡፡

የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 12 “የመንግስት አሰራርና ተጠያቂነት” በሚለው ርዕስ ስር ከተራ ቁጥር 1 ጀምሮ እስከ ተራ ቁጥር 3 ድረስ የተደነገጉት ሕግጋቶች ማናቸውም በመንግስታዊ ተግባራት ላይ የተሰማራ ሃይል በግልጽነትና በተጠያቂነት እንደሚመራ ይደነግጋል፡፡ ሁሉም የመንግስት ሹመኞችም ኃላፊነት በጎደለው መንፈስ ለሚፈጽሙት ተግባር በሕግ ፊት ተጠያቂ እንደሚሆን በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ከዚህ አኳያ ለምን አስተያየት ተሰጠብኝ የሚያዛልቅ ጉዞ አይሆንም፡፡

ወደ ዋናው ሃሳቤ ከመግባቴ በፊት ከነዚህ መሰረታዊ የሕገ-መንግስት ድንጋጌዎች በመነሳት፤ ከላይ ለጠቀስኳቸው ተቺዎቼ ሰለ ተጠያቂነትና “ስለውዳሴ ከንቱ” ጥቂት ነገር ማለት እፈልጋለሁ፡፡ ጥንታዊ ግሪኮች “ሂውብረስ” “Hubris” የሚሉት አንድ አቻ የማይገኝለት ስረው ቃል አላቸው፡፡ የእንግሊዘኛ ትርጉሙ  “Big headedness, Audacity, Arrogance ” ወይም  The Excessive Pride and Ambition that Usually Leads to the downfall of a Hero in Classical Tragedy” ይለዋል፡፡ አዛማጅ የአማርኛ ትርጉሙ ደግሞ “አጅግ በጣም መሰረቱን ከሳተ ማንአለብኝነት በሚመነጭ መንፈስ ላይ ተኮፍሶ  “ከከንቱ ውዳሴ” በስተቀር የልዩነት ሃሳብን ለማስተናገድ አቅም በማጣት  ለውድቀት የሚዳርግ ትምክህት” ይሆናል፡፡

ሕገ-መንግስቱ የሚደነግገው ሕገ-መንገስትን ስለሚያስከብርና ስለሚያከብር መከላከያ ሰራዊት እንደመሆኑ መጠን መከላከያ በሕገ-መንግስቱ ላይ በሰፈረው መሰረት እንደማንኛውም የመንግስት አስፈጻሚ አካል በሕግ ፊት ቀርቦ እንደሚጠየቅንና   በሚቀርቡት ሃሳቦችም ላይ ተመርኩዘው ለሚነሱ ትችቶች፣ ጥያቄዎችንና ለልዩነቶችን በራቸው ክፍት መሆን እንዳለበትና ሕገ-መንግስታዊ ግዴታ መሆኑን መረዳት ያሻል፡፡ ተቺዎቼ ግን  ከ“ውዳሴ ከንቱ” ከ“ማቆለጳጰስ” በስተቀር አማራጭ ሃሳብንም ሆነ ገንቢ አስተያየትን ለማስተናገድ ልቦናቸውን የደፈኑ ስለመሆናቸው ከጽሑፋቸው ለመረዳት ፈላስፍ መሆን አያሻውም፡፡

ለግንዛቤ እንዲረዳን እስኪ ሕገ-መንግስቱ በመከላከያ ሰራዊት መርሆዎች ዙርያ ስለሚደነግጋቸው ጉዳዮች ጥቂት ልበል፡፡ ሕገ-መንግስቱ በአንቀጽ 87 ላይ ከተራ ቁጥር 1 ጀምሮ እስከ 5 ድረስ የመከላከያ ሰራዊት የሚመራባቸውን መርሆዎች በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ የመከላከያ ሰራዊት የሃገራችንን

ሉአላዊነት ከማስከበር በተጨማሪ ሌሎች ማንኛውንም ዓይነት ሃላፊነቶችን ሊሰጠው የሚችለው ሕገ-መንግስቱ ውስጥ በሚደነገገው መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ( State of Emergency ) ተከትሎ ለሚፈጠሩ ግዳጆች ብቻ ነው፡፡ በሌሎች ማንኛውም ሃገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የመከላከያ አባላትና በዜግነታቸው መከላከያ በተቋምነቱ ከሚኖራቸው ሚና ውጭ፣ መንግስትን ወክለው በማናቸውም ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በራሱ ተነሳሽነትም ሆነ በመንግስት ፍላጎትና ጥያቄ ጣልቃ መግባት የሚያስችላቸው አንዳችም ሕገ-መንግስታዊ ክፍተት አልተጻፈም፡፡ በሕገ-መንግስቱ ላይ በተደነገገው መሰረት መከላከያ ሰራዊት እንደተቋም በሰላም ጊዜ በግል ዘርፉ መሸፈን የቻሉ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ጣልቃ መግብት ይቅርና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ( State of Emergency ) አዋጅ ባለበት ጊዜም ቢሆን መከላከያን ከሚመለከቱ ጉዳዮች ውጭ በማንኛውም የሲቪል ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተሳትፎው እንዲኖረው የተከፈተ በር የለም፡፡

ወደ ኢግዚቢሽኑ እንምጣ መንግስታዊ መገናኛ ብዙሃን በስፋት እንዳተቱት የመከላከያ ኢንጂነሪንግ በኢግዚቢሽኑ ላይ ያቀረባቸው የሲቪል ቁሳቁሶችና ምርቶች እንኳን ለግል ኢኮኖሚ ዘርፉ የሚተርፍ እውቀት ሊኖረው ይቅርና የመከላከያ ሰራዊቱን አባላትንም ቢሆን ከሚታወቀው ውጭ በዘመናዊና በላቀ ቴክኖሎጂና ሳይንስዊ ግኝት ላይ የተመሰረቱ የጦር መሳርያዎችን ለማስታጠቅ አቅም የፈጠረ መሆኑን የሚያሳዩ አልነበሩም፡፡

ለዚህ ደግሞ በመጀመርያ ደረጃ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ዛሬ የታጠቃቸው የጦር መሳርያዎች በኢግዚቢሽኑ ላይ ከቀረቡት በእጅግ የላቁና ዘመናዊ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለመገመት ይቻላል፡፡ ምናልባትም መከላከያ የታጠቃቸው የጦር መሳርያዎች የትውልድ(ፍብረካ) ዘመን (Generation) የቅርብ ጊዜ ከመሆናቸው የተነሳ አምራቾቹም ቢሆኑ የጦር መሳርያውቹን በግዢ ካልሆነ በስተቀር ለሚገጠጥሙ ድርጅቶች በሽያጭ የሚያቀርቧቸው ዓይነት እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡

በሌላ በኩል የመገጣጠም በሳይንሳዊ ፈጠራ ታግዞ ማምረት   በዕውቀት ዘርፍ አሰላለፋቸውም ሆነ በመሰረተ ሃሳብ ደረጃ የማይወራረሱ ለየቅል የሆኑ ስራዎች ናቸው፡፡ በኢግዚቢሽኑ ላይ የታዩት የተለያዩ የጦር መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎችና የቤትና የቢሮ ቁሳቁሶች ከ-እስከ ሳይባል የሜካኒካልም ሆነ የኤሌክሪቲካል ክፍላቸው፣ ዲዛየናቸውና ተገጣጣሚ አካላቶቻቸው በሙሉ ከአምራቾቹ ሃገራት በውጭ ምንዛሪ ተገዝተው የመጡ መሆናቸው በወቅቱ የነበሩት አስጎብኝዎቻችንም ቢሆኑ የደበቁት ጉዳይ አልነበረም፡፡ ከዚህ ተነስተን የምንደርስበት ድምዳሜ ቢኖር በእለቱ ከቀረቡት ምርቶች ውስጥ አንዱም በመከላከያ የጥናትና ምርምር መምሪያ አማካኝነት ተፈጥረው በሳይንስና ፈጠራ ምርቶች ባለቤትነት እውቅና ሰጭ  በሆነ ተቋምት አማካኝነት በፈጠራ መብት ባለቤትነት የተመዘገቡ ምርቶች አልነበሩም፡፡

ማንም ሊገምተው በሚችለው ደረጃ ስለቴክኖሎጂ ስናወራ ስለጥናትና ምርምር ወይም ስለፈጠራ ሳይንስና ስለመፈብረክ እያወራን መሆኑን ግልጽ ነው፡፡ የፈጠራ ሳይንስና የቴክኖሎጂ ፍብረካ በየትኛውም መለኪያ ከትንሹ ብሎን ጀምሮ እስከትልቁ ሞተርና ተገጣጣሚ አካላት ድረስ በውጭ ምንዛሪ በማስመጣት መገጣጠምን አያካትትም፡፡ ይህንን ለመረዳትም ሆነ ለማስረዳት ምንም ዓይነት እውቀትን  መጎናጸፍ አያስፈልገውም፡፡ ሲቀጥልም ተሽከርካሪ፣ ሞባይልና ኮምፒዩተርን አሁን ደግሞ ቴሌቪዥን መገጣጠም በኢትዮጵያዊያን ዘንድ ከዚህ ቀደም ያልነበረ እውቀትና አዲስ ግኝት ወይም ፈጠራ ተደርጎ መቅረቡ አስቂኝ ከመሆኑም በላይ ታሪክን እንደገና ለመጻፍ የሚደረግ ሽሚያ ከመሆን አይዘል፡፡ ለዘመናት የኖርንበት ተጨባጭ እውነታውም ይህንን አይፈቅድም፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ተሽከርካሪ የመገጣጠም ታሪክ ከበርካታ አስርት ዓመታት በፊት በአምቼ “ሀ” ብሎ ይጀምራል፡፡ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በመካከለኛ መጋዘንና በዘመናዊ ጋራዥ ውስጥ በመጀመርያ በሆላንድ ካርና በሊፋን ቀጥሎም በበላይ አብና በመስፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጅነሪንግ አማካኝነት መገጣጠም መቀጠሉ ዘመን የቆጠረ ታሪክ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ልቦና ሰጥቶት ላጤነው ተጠቃሾቹ የግል ዘርፍ (ከመስፍን ኢንዱስትሪያል በስተቀር) ድርጅቶች ተሽከርካሪ የ“መገጣጠም ታሪካቸው” ከመከላከያ ምሕንድስና በፊት ዓመታትን ያስቆጠሩ መሆናቸው አስጣ አገባ የሚያስከትል ነገር የለውም፡፡

“ተሽከርካሪ የመገጣጠም” ታሪካችን መነሻው ይህ ከሆነ ደግሞ በእውቀት ሽግግርም ሆነ በልምድ ልውውጥ ቀዳሚዎቹ ተሽከርካሪ ገጣጣሚዎች ከመከላከያ ምሕንድስና የሚማሩት ነገር ሊኖር እንደማይችል ዘመን የቆጠረ ተመክሯቸው ምስክር ነው፡፡ እንደውም የመማር ነገር ከተነሳ መማር ያለበት መከላከያ ምሕንድስና ለመሆኑን በርካታ ጠቋሚ ጉዳዮች ማንሳት ይቻላል፡፡ ቢያንስ ቀደምቶቹ የተሽከርካሪ መገጣጣሚያ ድርጅቶች በየመንገዱ በሚቆሙ ተሽከርካሪዎች ምክንያት አስካሁን ሲታሙ አልሰማንም፡፡

ሞባይል መገጣጠምን በሚመለከት በአሁኑ ጊዜ ከሦስት ያላነሱ ሞባይል የሚገጣጥሙ ድርጅቶች፣ ሞባይልን በብቃት እያመረቱ ለገበያ በማቅርብ ውጤታማ ስራ እየሰሩ እንደሆነ የከተማችን ወሬ ከሆነ ሰንብቷል፡፡ ኮምፒየተር መገጣጠምን በሚመለከትም ከዚህ ቀደም በርካታ ድርጅቶች እንደነበሩና አሁንም ኮምፒዩተር ለመገጣጠም በዝግጅት ላይ ያሉ በርካታ የግል ዘርፉ ባለሟሎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ቴሌቪዢንም ቢሆን ከቬስቴል

ጀምሮ እስከ ሳምሳንግ ምርቶች መዝለቅ ይቻላል፡፡ እንግዲህ በግርድፉ፤ እውነታው ይህን ከመሰለ የመከላከያ ምሕንድስና እነማንን የአዲስ ቴክኖሎጂ ባለቤት ለማድረግ አቅዶ በግሉ ዘርፉ ሊሸፈኑ በሚችሉ ስራዎች ውስጥ ጣልቃ መግባት እንዳስፈለገው ማብራሪያ ሊሰጠን ይገባል፡፡

እዚህ ላይ ቆም ብለን በርካታ ጥያቄ ማንሳት ይኖርብናል፡፡ የግል ዘርፉ አቅም ሳያንሰውና ከተቋቋሙት ፋብሪካዎችም በላይ በርካታዎቹ ወደ ገበያ በስፋት በመግባት ላይ እንደሆኑ እየታወቀ የመከላከያ ኢንዱስትሪ በመንግስት አቅምና ከግብር ገቢ በሚሰበሰብ በጀት እየታገዘ በነዚህ ዘርፎች ውስጥ ጣልቃ መግባት ለምን አስፈለገው? ሁለተኛው እንደው አስፈላጊ ነው ቢባል እንኳን ኢትዮጵያ ቅድሚያ የምትሰጣቸው በርካታ ሕዝባዊና ሃገርዊ የልማት ጥያቄዎች እያሉ ተሸከርካሪዎችንና ሞባይሎችን መገጣጠም የመከላከያን ዓይንና ጆሮ ወይም ትኩረት እንዴት ሊስብ ቻለ? ወይስ የግል ዘርፉ ልማታዊነት ስለሚንሰው በልማታዊ ስም መንግስታዊ ከበርቴነትን ለማስፈን? ሦስተኛው መከላከያ ገቢው የተመሰረተው ከትርፍ ከሚገኝ ፈሰስ መሆኑ ያታወቃል፡፡ እውነታው ይህ ከሆነ መከላከያ የተመሰረተበት እርሾ ከየት ፈሰስ ተደረገ? ከምሰረታው በኃላስ የመከላከያ ምሕንድስና ገቢና ወጭው በማን ቁጥጥርና ክትትል ስር ይገኛል? ለብክንት፣ ለሙስና፣ ለአምቻ ጋብቻና ለመጠቃቀሚያ አለመጋለጡንስ በሚመለከት ማን ማረጋገጫ ማቅረብ ይችላል? ወዘተርፈ …

## Part 2

በአጠቃላይ የመከላከያ ኢንዱስትሪው የግል ዘርፉ በብቃት ሊሸፍናቸው ባልቻላቸውና እየሸፈናቸው በሚገኙ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መንግስትን ተገን አድርጎ በመንግስት ፓራስታታልነት (Parastatal) ከግብር በሚገኝ በጀት ጡንቻውን አፈርጥሞ ግዙፍ አቅም በመገንባት ውድድር ውስጥ መግባቱ በመቻሉ የግል ዘርፉን እያዳከመ መሆኑ እየታየ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ መከላከያ ምሕንድስና አሁን በተጀመረውና መንገድ ቀጥሎ በሆቴል፣ በብረታ ብረትና በባንክ፣ በሸቀጣ ሸቀጥና በቁሳቁስ ማምረቻ ስራዎችና በሌሎቹ የግል ኢኮኖሚ ዘርፉ ውጤታማ በሆነባቸው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በጥልቀት መግባቱና ለመግባት ማቀዱ መንግሰት በመከላከያ ምሕንድስ ፓራሳታታልነት ታግዞ የነጻ ገበያ ውድድሩን በማዳከም እራሱን ብቸኛው አቅራቢ  በማድረግ ገበያውን ርስቱ፤ ተገልጋዩን ጥገኛው እያደረገ መሆኑን መገምት ይቻላል፡፡  ደርግ  በኮርፖሬሽኖቹና በጥገኞቹ አማካኝነት ከወጥ አቅም ሳይቀረው ሲቸረችር ኖሯል፡፡ አማራጭ በሌለበትም አጉል አምልኮ የተለመደ በመሆኑ ዜጎች አማራጭ በማጣት ካለአንተ በጎ ፈቃድ መኖር አንችልም እስኪሉ ሲያንበረክክ መኖሩ አሌ የሚባል አይደለም፡፡ ዛሬስ ምን ተያዞ ጎዞ ላይ ነን!? በመግቢያዬ ላይ በጥቅስ እንዳስቀመጥኩት አልጄርያውያን ውሎ አድሮ የገጠማቸው ውጥንቅጥና ተረት  እስከመተረት ያደረሳቸው ፈተና ይህው ነበር፡፡ በወቅቱ አልጄርያውያን እንደ ሃገር መከላከያ ይኖራቸው ወይም ሃገራቸው የመከላከያው ትሁን ለመለየት እስከመቸገር ደርሰው ነበር፡፡

አማራጩ ምንድን ነው? አማራጩ ውስብስብ አይደለም፡፡  የመከላከያ ኢንዱስትሪው ሕገ-መንግስቱ ውስጥ የሰፈሩት ድንጋጌዎች የሁላችንም የበላይ መሆናቸውን በቅድሚ በተግባር ማስመስከር አለበት፡፡ ቀጥሎም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚን የማሳደግና የማበልጸግ ፋላጎተና ጉጉት ካለውና አልፎ ተርፎም ሁኔታው የግድ የሚልበት ሁኔታ ከተፈጠረ ቅድሚያ ለሚሰጠው ቅድሚያ መስጠት ያሻል፡፡ ዛሬ ኢኮኖሚያችን ያለበት ክፍተትና ችግር ተሽከርካሪ፣ ሞባይልና ኮምፒዩተርና ቴሌቪዥን ከመገጣጠም ወይም ከሆቴል፣ ከባንኪንግ፣ ከቁሳቁስ ምርቶች ፍጆታ በላይ እጅግ ግዙፍና ውስብስብ መሆኑን ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡ የመከላከያ ምሕንድስናና አባላትን ጊዜ፣ የግብር ከፋዩን ገንዘብና የመንግስትን ጉልበት ሕገ-መንግስታዊ እውቅና ባለው ጉዳይ ላይ ብቻ ማተኮር ይገባል፡፡

ሌላው በመግቢያዬ ላይ ያነሳሁት ጉዳይ መከላከያ ከየትኛውም የፖለቲካ አስተሳሰብ ጋር ሳይወግን ሕገ-መንግስቱን የማክበርና የማስከበር ተልዕኮ ሁነኛ ስራው መሆኑ በትችቶቹ አቅራቢዎችና በመገናኛ ብዙሃን ተደጋግሞ የማደመጣችን ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ ከነዚሁ ጸሐፊዎች “መከላከያ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመርን ያረጋገጠ ነው፡፡” ማለታቸው አስደንቆኛል፡፡ የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ “87″ “የመከላከያ መርሆዎች” በሚለው ርዕስ ስር ተራ ቁጥር 1  ላይ መከላከያ ሰራዊት ከየትኛውም የፖለቲካ ፍለስፍና ወይም ፓርቲ እራሱን ነፃ ማደረግ ያለበት መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በዚሁ ርዕስ ስር ቁጥር “4″ ላይ ደግሞ የመከላከያ ሰራዊት በማንኛውም ጊዜ ለሕገ-መንግስቱ ተገዢ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከላይ እንደነሳሁትና ከጽሁፎች ላይ ለመረዳት እንደቻልኩት መከላከያ ሰራዊት የአብዮታዊ ዴሞክራሲን መስመርን ለማረጋገጥ የቆመ ሰራዊት ከሆነ፤ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በነጻና ገለልተኛ ምርጫ ቢሸነፍ ሰራዊቱ ከማን ጋር ሊወግን ይሆን? ለ50 ዓመታት ኢትዮጵያን ለማስተዳደር እቅድ ካለው ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋር ወይስ በነጻና ገለልተኛ ምርጫ ከአሸነፈው ሃይል ጋር?  ወይስ ከሕገ-መንግስታዊ ተግባሩ እራሱን ያገላል? ይህ ጉዳይ መልስ የሚሻ የሕገ-መንግስት፣ የስርዓትና የሕግ የበላይነት ጥያቄን በውስጤ ያዘለ ጉዳይ ነው፡፡ መከላከያ መልሱ ዝምታ ከሆነ ግን የመከላከያ ምሕድስና ኢኮኖሚያዊ ጣልቃ ገብነቱ ሌላ ሳይሆን

“ርዕዮተ ዓለማዊ” መሆኑን ለመጠርጠር እንገደዳለን፡፡ ይህ ደግሞ በተለይ የግል ኢኮኖሚ ዘርፉ እራሱን ከመንግስት ጥገኝነት ሙሉ ለሙሉ አላቆ ወደ መካከለኛና ከፍተኛ ገቢ በስፋት በመሸጋገር፤ በራስ መተማመን ፈጥሮ የምርጫ ውጤትን ለማስለወጥ የሚችል ወሳኝ ሃይል እንዳይሆን የተደቀነበት ፈተና ስለመሆኑ አመላካች ርዕስ ይሆናል፡፡

ሌላው ከላይ ያነሳሁት ጉዳይ የመከላከያ ምሕንድስ የመመስረቻ፣ የስራ ማስኪጂያ መዋእለንዋይ ፈሰስ የሆነበትና የወጭና ትርፍ አያያዙ ዝርዝር ጉዳይ ነው፡፡ “መከላከያ ምሕንድስና የተቋቋመው ከመከላከያ በጀት ተቆጥቦ ነው፡፡” የሚለው የተቺዎቹ ትንታኔ በመደበኛ የሂሳብ ስሌት አማካኝነት ማወራረድ ተአምርን የሚጠይቅ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ስለመከላከያያ በጀት ጉዳይ በተወካዮች ምክር ቤት አማካኝነት የተሰጡን ትንታኔዎችን እንዳዳመጥነው ለመከላከያ የሚመደበው በጀት ከመከላከያ ሰራዊት የእለት ተዕለት ስራ ማስኬጃያ፣ ደሞዝ፣ ጥገናና የመሳርያ ግዢ በላይ ሊተርፈውና መከላከያ ምሕንድስናን ለማቋቋም የማይስችል መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ሃሳብ ስንነሳ “መከላከያ ምሕንድስና የተቋቋመው ከመከላከያ በጀት ተቆጥቦ ነው፡፡” የሚለው አቀራረብ በቁጠባ ላይ ቁጠባ እንዴት ሊሆን ይችላል የሚለውን ጥያቄ እንድናነሳ ያስገድደናል፡፡ ከዚህ ተነስተን የምንደርስበት ድምዳሜም ስጋታችን ወደ ጥያቄ እንድንለውጥ የሚያስገድድ ነው፡፡

በአጠቃሌ የመከላከያ በጀትን በሚመለከት አስከአሁን የምናውቀው እውነታ በቁጠባ ላይ ቁጠባ አደርጎ ግዙፍ ፋብሪካን ከማቋቋም ትረካ ጋር በእጅጉ የሚራራቅና አብሮ የማይሄድ መሆኑን ነው፡፡ በተለያየ ጊዜ ባዳመጥነው በተወካዮች ምክር ቤት ዘገባ መሰረትም የመከላከያ በጀት ከአጠቃላይ የሃገሪቱ በጀት የሦስት ፐርሰንት ሽፋን ብቻ ያለው መሆኑን ነው፡፡ ተያይዞም በዚህም ምክንያት የበጀቱ ድልድል ለሰራዊቱ ፍጆታ በአስተማማኝ ሁኔታ በቂ ስላልሆነ መከላከያ በጀቱን ወጭ ቆጣቢ በሆነ መንገድ የሚስተዳድር እንደሆነ ተገልጾልናል ፡፡ እውነታው ይህ ከሆነ መከላከያ በቁጠባ ከሚመራው በጀት ላይ እደገና ሌላ ቁጠባ አድርጎ ለመከላከያ ምሕንድስና ምስረታ  ምሰሶ ሊሆን እንዴት ይችላል? በቁጠባ ላይ ቁጠባ ድንቅ የሆነ ጥበብና ክህሎት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ አሊያም ከባለቤቱ ያወቀ… እንዲሉ የመከላከያ ምሕንድስናን የምስረታ በጀቱን በሚመለከት ሌላ እውነታን መፈለግ ይኖርብናል ማለት ነው፡፡

ይህ ካልሆነ ደግሞ የተወካዮች ምክር ቤት በጀቱን እንደገና ሊመረምር ይገባዋል፡፡ አስካሁን የመከላከያ ምሕንድስና የበጀት ምንጭ፣ ወጭና ገቢ በግልጽ በኦዲተር ተመርምሮ ሪፖርት ቀርቦ አያውቅም፡፡ በዚህ ምክንያት ገቢውንም ሆነ ወጭውን ለማወቅ አዳጋች ነው፡፡ ማንኛውም በሕዝብ ሃብት የሚንቀሳቀስ መንግስታዊ ተቋም ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ለሚመለከተው አካል ግልጽ ሆኖ መቅረቡ የሚያጠያይቅ ጉዳይ የለውም፡፡ በእኔ እምነት ለግልጽነትና ተጠያቂነት ሲባል ማንኛውም መንግስታዊ ተቋም በሰራው ስራ ልክ መገምገም አለበት፡፡ ግምገማውም በሕዝብ ፊት ቀርቦ በስራው ሂደት ድል ከቀናው ድሉን ማጣጣም ድክመትም ካለበት ድክመቱን ተቀብሎ ለሚመጣው ሁሉ ዝግጁነትና ቆራጥነት ሊኖረው ይገባል፡፡

ሌላው ላነሳው የምፈልገው ጉዳይ ከላይ የጀመርኩትና በእንጥልጥል የተውኩት የመከላከያ ሰራዊት ሳምንት በሚል ርዕስ ስር የቀረበው ኢግዚቢሽንን የሚመለከተው ጉዳይ ነው፡፡ ልዩነቶቼ እንደተጠበቁ ሆነው ከኢግዚቢሽኑ ሂደት ላይ ስለአንዳንድ ጉዳዮች ለመረዳት እንደቻልኩት መከላከያ በሕገ-መንግስቱ የተሰጡትን ኃላፊነቶች በብቃት ለመወጣትም ሆነ ለማስፈጸም የሚያደርገውን ጥረት የምደግፍና የማምነበት መሆኑን አስምሬበት ለማለፍ እፈልጋለሁ፡፡ የተለያዩ ሃገራት መከላከያ ሰራዊት  ሕገ-መንግስቱ በሚፈቅድላቸው ልክ ሃገራዊ ኢኮኖሚ በመገንባታ ሂደት ላይ በጎ ሚና ለመጫወት ምክንያት እንደነበሩ በርካታ ተሞክሮዎች እንዳሉም አውቃለሁ፡፡ በእኔ እምነት በተለይ ከፍተኛ ወጭን በሚጠይቁና በግል ዘርፉ አቅምም ሆነ ተነሳሽነት ሊሸፈኑ በማይችሉ ነገር ግን ከሃገርና ከሕዝብ ደህንነት ጋር ግንኙነት ባላቸውና መከላከያን በሳይንስና በቴክኖሎጂ ውጤቶች የማዘመን ስራዎች ላይ መከላከያ ገንቢ ሚና ሊኖረው ይገባል፡፡

ይህም ሆኖ እንደዚህ ዓይነቱ ኃላፊነትና ግዳጅ ለመከላከያ የሚሰጠው ከቀሪዎቹ ዜጎች የመጠቀ እውቀትና ለሃገር ተቆርቆሪነት በመከላከያ ዘንድ እንዳለ ከማሰብ መንጭቶ ሊሆን አይገባውም፡፡ መነሻም መሆን ያለበት ጉዳዮ የክህሎትና የመንግስታዊ ቀጥተኛ ተሳትፎ የመከላከያን ሙያና ጣልቃ ገብነት የሚሹ ጉዳዮች ስለሚደርጉትና በተለይ ደግሞ የግል ኢኮኖሚ ዘርፉ አቅም ስለሌለው ብቻ መሆኑ አለበት፡፡ ቀጥሎም ይህ ሚናቸው ወደ ተግባር የሚሸጋገረው የጉዳዩ ዋነኛ ባለቤት በሆነው ሕዝብ ይሁንታ ላይ ተመስርቶ ሕገ-መንግስቱን በማይጻረርና ከሕገ መንግስቱ በሚመነጭ ስልጣንንና ሃላፊነት ላይ ብቻ ተመርኩዞ መሆኑ አለበት፡፡

መከላከያ መንግስታዊ ተቋም እንደመሆኑ መጠን የሃገርንና የሕዝብን ደህንንት የማስከበር ከፍተኛ ሕዝባዊና ሃገራዊ ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ ለዚህ የሚመጥን ዝግጅትና ቁመና መፍጠሩ ደግሞ ቀላል ተግባር እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በክህሎት ላይ የተመሰረተ እውቀት፣ ብቃትና  ከፍተኛ ወጭን ይጠይቃል፡፡ ይህ ወጭ የሚሸፈነው ከግል ዘርፉ ከሚገኝ የተለያየ ገቢ እንደመሆኑ መጠን የግል ዘርፉን የማይጎዳና የማያዳክም መሆን አለበት፡፡ በተለይ ደግሞ የዜጎችና የሃገር ደህንነት ከማረጋገጥ አኳያ የሚያስፈልጉ የቴክኖሎጂና የሳይንስ ውጤቶችን ከማጎልበት አንጻር ብቻ መቃኘት ይገባዋል፡፡ ስለዚህ በግሌ ያለኝ አቋም መከላከያ በግል ዘርፉ በሚሸፈኑ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ዙርያ የሚያደርገው ጣልቃ ገብነት በመጀመርያ ከመርህ አኳያ

የማልደገፈው ከመሆኑም በላይ መከላከያ ከተቋቋመበት ዓላማና በሕገ-መንግስቱ ከተሰጡት መርሆዎች ውጭ እንዲሆን ስለሚያደርጉት ሁላችንም ትኩረት ልንሰጠው የሚገባ ጉዳይ መሆኑን አምንበታለሁ፡፡ የማንም ሃገር መከላከያ ሰራዊት አባላት የሃገርና የዜጎችን ደህንነት (ፖሊስ፣ደህንነት ጨምሮ) የሚከታተሉት ከዜጎች የሚለያቸው ነገር ስላለ ሊሆን አይችልም፡፡ ነገር ግን ከማንኛውም የፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻ ሆነው ሕገ-መንግስቱን ለማክበርም ሆነ ለማስከበር እንዲችሉ የተለየ ኃላፊነት በሕገ- መንግስቱ ስለሚጣልባቸው ሲሆን በዚህም ምክንያት ተቋማቱ ገለልተኛ ሆነው ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱና ሃገረቱ እንዳትናጋ ዘብ የመቆመ እድላቸው ከዜጎች በላይ ጥልቅ ስለሚያደርገው ነው፡፡

ዴሞክራሲያዊ ስርዓታችን፣ የሃገራችን ሉዓላዊነትና የሕዝባችን ደሕንነት ያለማወላወል መከበር እንዳለበት አምናለሁ፡፡ ለዚህ ተግባር የሚያስፈልገን የመከላከያ ሃይል ከአቅማችን በላይ ያልገዘፈ ወይም ከሚያስፈልገው በታች ያላነሰ መሆን ይገባዋል፡፡ ከዚህ ውጭ መከላከያ ሰራዊት በአንድም ሰው ሆነ በአንድ ብር ከሚፈለገው በላይ ተጨማሪ አቅም ሊኖረን አይገባም፡፡ ከዚህም መርህ ስንነሳ መከላከያ በኢኮኖሚውም ሆነ በሌላው ዘርፍ ከሕገ-መንግስቱና ስርዓቱ ከሚፈቅደውውጭ መጎልበቱ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓቱም ሆነ ለመልካም አስተዳደር እንዲሁም ለዜጎች ኢኮኖሚያዊ ነጻነት አደጋ ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ መገንዘብ ብልህነት ነው፡፡ በዓለማችን ላይ የሚገኙ የመከላከያ ሰራዊት ሃይሎች በበጀት እንዲተዳደሩ የሚያስፈልግውም በዚህ ምክንያት መሆኑ ዓለማ አቀፍ አውነታ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ መከላከያ ከበጀቱ ውጭ የሚያደርጋቸው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ከሕዝብ ዓይንና ጆሮ ውጭ መሆን የለባቸውም፡፡ ከሕዝብ ዓይንና ጆሮ ውጭ ከሆኑ ደግሞ በዴሞክራሲያዊ ስርዓቱም ላይ ሆነ በሃገራዊ ሃብት አጠቃቀም ላይ ያልተገባ ተጽእኖ ሊኖራቸው እንደሚችል ከወዲሁ መረዳት ያሻል ፡፡

የተለያዩ ልማታዊ መንግስታት ወይም በቀጥተኛ አጠራራቸው "መንግስታዊ ከበርቴዎች" በሃገራዊ ሃብት አጠቃቀምና በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ወሳኝ ሚና ከሚሰጧቸው "ፓራሳስታታል" (Parastatal) ወይም መንግስታዊ የእጅ አዙር ተቀጥላት ተቋምት መካከል አንዱና ወሳኙ ሃይል መከላከያ ነው፡፡ ይህ የሚሆነበት መሸረታ ምክንያጽ ደግሞ ከላይ ከዘረዘርኩት በተጨማሪ መከላከያ ሰራዊት ከቀሪው ዜጋ የሚለየውና እራሱን የሚያበቃበት ስልጣና ስላለውና ስልጠናው ደግሞ በትጥቅ የታጀበ በመሆኑ ግዙፍ አቅሙን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ይህ አቅም በልክ ካልተሰፈረ መከላከያ ለዜጎች ዴሞክራሲያዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መብቶች ዘብ ከመቆም ይልቅ መብቶቻቸውን ለመገዳደር ያልተጋባ በርና እድል የሚከፍትለት መሆኑ ይታወቃል፡፡

እንደ መከላከያ ያለ ተቋም ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴን በመቆጣጠር አቅሙ ጎልብቶ እንዲወጣ ከተደረገ ዴሞክራሲን በመገደብና መብትን በመጻረር ከአምባገነን ሃይሎች ጋር ተሰልፎ መንግስት አንጋሽ (king Maker) ሊሆን እንደሚችል ከግብጽ፣ ከአልጄሪያ፣ ከፓኪስታንና ከሌሎቹም እልፍ ሃገራት ተሞክሮና ትምህርት መውሰድ ይቻላል፡፡ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ ዜጎች ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ሰብአዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ መብቶቻቸው የሚረጋገጠውና ጥበቃ የሚያገኘው በሕገ-መንግስቱ ዋስትናነት እንጂ በመንግስትም ሆነ በመከላከያ ወይም በሌሎች ተቋማት ውስጥ በሚገኙ ግለሰቦችና ጀግኖች ላይ በመተማመን እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡

የሚሊተሪ ተቋማት እንደ ሂትለርና ሙሶሎኒ ያሉ ፋሺስቶችንና ሌሎች በርካታ አምባገነኖችን የተፋለሙ አኩሪ ሰዎችን እንደፈጠረ ሁሉ እንደነ ኢዲ አሚን፣ ሙባረክ፣ ሳዳትና መንግስቱ ሃይለማርያም ያሉ ለሰው ልጆች ማፈርያ የሆኑ ግለሰቦችን መፍጠሩን ልንዘነጋ አይገባም፡፡ የዓለም ታሪክ ይህንን እውነታ እንደማይዘነጋውም እርግጠኛ ነኝ፡፡ መንግስታዊ በሆኑ የመከላከያም ሆነ ሌሎች የዴሞክራሲ አሊያም ልማታዊ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦች፣ ግለሰብ እንደመሆናቸው መጠን ሊሸከሙት ከሚችሉት በላይ ስልጣንም ሆነ ሃይል ሲቀዳጁም ወይም በሃገራዊ ሃብት ላይ እንዲያዙ ፈቃድ ሲሰጣቸው ውሎ አድሮ ስርዓታችን ማጣፊያው ወደሌለው ውጥንቅጥ ውስጥ ሊከተን ይችላል፡፡

ማንኛውም ምድራዊ ሃይል ለስልጣኑ ገድብና ልክ ያስፈልገዋል፡፡ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትና ሕገ-መንግስት ደግሞ የዚህ ገደብ ሽምቀቆ ናቸው፡፡ ሕግ-መንግስት የዜጎች ኢኮኖሚያዊም ሆነ ሰብአዊ ወይም ዴሞክራሲዊ መብት እንዳይጣስ ከለላ ይሰጣል፤ ጥብቃም ያደረጋል፡፡ ዓለማችን በመለኮታዊ ንግስና የምትመራበት ዘመን ጀምበሩ ካዘቀዘቀ በርካታ አስርት ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ የእመኑን፣ ተቀበሉን፣ ችግር የለውም፡፡ አሊያም ለሃገርና ለሕዝብ ጥቅም ስለምንሰራ አትመርምሩንና አትፈትሹን ዜማ ቀኑ ሊመሸበትና በሕዝብ የበላይነት፣ በግልጽነትና ተጠያቂነት መንፈስ ሊተካ ይገባዋል፡፡

ከዘመናት ፍልሚያ በኃላ የ "ይስሙላ ሶሻሊዝም" እንዳይመለስ ሆኖ ቢንኮታኮትም ዛሬ በዘመናችን ለዴሞክራሲያዊ ስርዓትና ለሕዝብ ይሁንታ ከባድ ማነቆ ሆኖ ከተሰለፉት ውስጥ አንዱና ዋነኛውን ቅሪቱ የሆነውንና በልማታዊነት ስም የሶሻሊዝምን ካባ ያጠለቀውን የ"መንግስታዊ ከበርቴነት" ስርዓት ተክቶ መሄዱ ነው ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢህአዴግም የዚህ ስርዓት ከባድ አሻራ እየታየበት ነው፡፡ ሃገራዊ ባለሃብትን ከማጠናከር ይልቅ እያዳከሙ የግል ባለሃብቱ ማልማት አልቻለም በሚል መፈክር ስም ከሞባይል ጀምሮ እስከ ተሸከርካሪ መገጣጠም ድረስ ሁሉንም ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች በፓራስታታሎች ((Parastatal) መቆጣጠረርና ማውረስም ዘለግ ሲልም በችሮታ መልክ መስጠትና ቅድሚያ ለመንግስት ማለት "መንግስታዊ ከበርቴነት"ን ለማሳደግ ከሚሻ አዕምሮ የሚመነጭ አስተሳስብ ከመሆን ውጭ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም፡፡

በአሁኑ ወቅት በሃገራችን ለመገንባት ያቀድነው የነጻ ገበያ ወይም የውድድር ስርዓት “መንግስታዊ ከበርቴነት”( State Capitalism) አጥልቶበታል፡፡ የኢህአዴግ መንግስታዊ ከበርቴነት በፓራስታታሎች በመታገዝ ሁሉን በጉያው በመጠቅለል በአቅምና በሃብት እጥረት እየተሰቃየ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የሚከሰት የአቅም እጥረትን፣ ትኩረት በሚስቡ እንቅስቃሴዎች በመጠመድ፣ በሃብት እንደተንቆጠቆጡ ሃገሮች የመጨረሻው ግቡ በማይታወቅ ሁኔታ መንገድ እያፈረሱ መንገድ መገንባትን፣ በልማታዊነትና በአውቅልሃለሁ ጥላ ስር ሆኖ በአስገዳጅ ቁጠባ የግል ዘርፉን ማዳከምን፣ የውጭ ምንዛሪን ብቸኛ ተጠቃሚ መሆንን ሁነኛ ሚናው አድርጎታል፡፡ በተለይ ደግሞ ቅድሚ ለ“መንግስታዊ የልማት እንቅስቃሴ ” በሚለው የዚህ ፍልስፍና የመገለጫዎች አማካኝነት የመከላከያ ኢንዱስትሪውና ሌሎቹ የፓራስታታሎቹን ወይም የጥገኞቹን ጣልቃ ገብነት እያጣናከረ ቀድሞውንም በስጋትና በሰቆቃ የነበረውንና ጫና የበዛበትን የግል ዘርፉን በጥርታሬ እንዲታይ መንስኤ በመሆን፣ አቅሙ ከሚችለው በላይ በመዋጮና በግብር አልፎ ተርፎም ለእድገት የሚስፈልገውን ወረት በአስገዳጅ ቁጠባ በመቀራመት ባለሃበቱን ስደተኛ፣ ግለሰብ ነጋዴውን ሽባ በአጠቃላይ የግል ዘርፉን እርባና ቢስ እያደረገው ይገኛል፡፡

በግል ዘርፉ ክፍተት ባልታየባቸው የስራ መስኮች በፓራስታታሎቹ (Parastatal) ወይም በመንግስታዊ ተቀጥላዎች (ንግድ ባንክን ጨምሮ) አማካኝነት ከግብር ከፋዩ የሚሰበሰበውን ሃብት እየተደራጁበትና የግል ዘርፉን ከውድድር ውጭ  እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን  ተመቻችተዋል፡፡ ይህ ደግሞ በአጭር ጊዜ ትርፋማ ቢመስልም በሂደት በተቋማቱ ላይ ሊኖር የሚገባውን ሕዝብዊነትንና ድጋፍ የሚረሽር ከመሆኑ በስተቀር የሚሰጠው አንድችም ፋይዳ አይኖርም፡፡ በተለያዩ ሃገሮችም እንደታየው አጠቃላይ ውጤቱ የግለሰብና የቦታ ሽግሽግ ከመሆን አያልፍም፡፡ ይህ ደግሞ ግለሰብ ነጋዴውን በመንግስታዊ ከበርቴና በተቀጥላ ተቋማት ወይም በመንግስታዊ ነጋዴዎች መተካት በማስከተል ኢኮኖሚ ውድድርና በመግደል የሸኩቻ፣ የሙስናና የጡንቻ ማሳያ በማድረግ ለእድገታችን ጠር መሆኑ የሚጠበቅ ነው፡፡

ባለፉት ሃያና ሰላሳ ዓመታት የአልጀርያ ሕዝብ ቁጭ ብሉ የሰቀለውን የመከላከያ ሃይል ቆሞ ማውረድ ሲያቅተው ለመታዘብ ችለናል፡፡ ፓኪስታን ግብጽና ሌሎችንም ሃገሮችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከወዲሁ መተራረምና ከግለሰቦች ይልቅ ለሕገ-መንግስትና ለስርዓት ታማኝ መሆን ለሁላችንም የሚበጅ ምቹ መንገድ ነው፡፡ መከላከያ አቋሙን ለመገንባት እንዲችል ሕገ-መንግስቱ በርካታ ኃላፊነቶችንና እድሎችን አጎናጽፎታል፡፡ እነዚህ ወሳኝ ሃገራዊ ሚናዎቹን ለማጠናከር የመከላከልና የማጥቃት ብቃቱን የሚያጎለብቱ ቴክኖሎጂም ሆነ እውቀት ቀመስ ስራዎችን መስራቱ ያስማማናል፡፡ ከነዚህ ወሳኝ ሚናዎቹ በኋላ የሚተርፈው ጊዜ ካለ (እሱንም ቢሆን እጠራረራለሁ፡፡) የግል ዘርፉን የማያዳክሙና ከጫወታ ውጭ  የማያደርጉ በርካታ ስራዎች አሉ፡፡ መከላከያ ሕገ-መንግስቱን ለማክበርም ሆነ ለማስከበር ተሸከርክሪ፣ ሞባይልና ቲቪ መገጣጠም አለበት የሚለው ክርክር ለማንም ሊዋጥ የሚችል አይደለም፡፡ ከሕገ-መንግስቱም ሆነ ከነጻ ገበያ ወይም ከውድድር ስርዓት ጋር ይጋጫል፡፡ በሂደትም ሕዝበዊነትን ይሸረሽራል፡፡ አልፎ ተርፎም ለሙስና ለብክነትና ላልተገባ ብልጽግና ያጋልጥል፡፡ ለሕገ-መንግስታችንና ሉዐላዊነታችን የሕዝብ ጥበቃ እንደሚያሻን ሁሉ መከላከያ ምሕንድስና ከተሳሳተ መንገድ እንዲወጣ የሕዝብ ዓይንና ጆሮ ያስፈልገዋል፡፡